*Made for minds.*

# የሥነ ምግባር ደንብ

## እሴቶቻችን፤ አመለካከታችን፤ እርምጃችን

# እሴቶቻችንን
# መኖር





ውድ ባልደረቦቼ፣

ዶቼ ቬለ (DW) ባሁኑ ወቅት፣ ከዚሕ ቀደም ከነ
በረዉ በላቀ ሁኔታ በርካታ ሕዝብ የሚከታተለዉ፤
እንደ ገለልተኛ ድምፅ ከፍተኛ ተአማኒነትና ክብር
ያተረፈ መገናኛ ዘዴ ነዉ። እኛ በተለይ የመና
ገር ነፃነታቸዉ ለተገደበባቸዉና ለፕሮፓጋንዳ ለተ
ጋለጡ ሰዎች መረጃ አሰራጭ መሆን እን ፈል
ጋለን።

## በመላዉ ዓለም መረጃዎች በነፃነት የሚሰራጩበትንና የመናገር ነጻነት የሚጠናከሩባቸዉን ሁኔታዎች እናበረ ታታለን።

እኛ፣ የDW ሠራተኞች በሙሉ አንድ ርዕይ እን
ጋራለን፡ ነጻነት፣ የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣
ከፍተኛ የሥነምግባር ደረጃ ዴሞክራሲና የሕግ
የበላይነት፣ ክፍትነት፣ መቻቻልና ሕዝብን በግ
ልጽነት ማገልገል። ጥረታችን እነዚህን ተግባ
ራዊ ለማድረግ ነው። ለዚሕም ነዉ፣ የፆታ የበላይ
ነትን፣ ዘረኝነትን፣ ፀረ-ሴማዊነትን ጨምሮ ማንኛ
ዉንም አድልዎ የምንቃወመዉ። ጀርመን ያለባት
ታሪካዊ ኃላፊነትም የእስራኤን የመኖር መብት
(ሕልዉና) እንድንደግፍ ያደርገናል። ለነዚሕ
እሴቶች ተገዢዎች ነን። ይሕ፣ በምንሠራቸው
ዘገባዎች ይዘት፣ በ DW Akademie የማጎ
ልበቻ ፕሮጀክቶችና በትምህርታዊ ፕሮግራ ሞች
ብቻ ሳይሆን ከ160 ከሚበልጡ ሐገራት ተወላጅ
የሆኑ ባልደረቦቻችን የዕለት ከዕለት ግንኙነትም
ይንፀባረቃል።

የሕዝብ አደራ እንደተሸከመ ዓለም አቀፍ
የመገናኛ ዘዴ ተቋም፣ ለተጠቃሚዎች፣ለፕሮጀክ
ት፣ለሸያጭና ለንግድ ሸሪኮቻችን፣ ለማኅበረሰብ
እንዲሁም ለአካባቢ ጥበቃ ልዩ ኃላፊነት አለብን፡
፡ይህ የሥነምግባር ደንብ እነዚህን ኃላፊነቶችን
በውስጥና በውጭ ግንኙነቶቻችን ገቢራዊ የምና
ደርግበትን ስልት ያብራራል።

የሥነ ምግባር ደንቡ ሁሉን አቀፍና ገዢ
በመሆኑ፣ እርስ በእርስ ባለን ግንኙነት እና
የሥራ ኃላፊነት በየቀኑ የምንተገብራቸውን አስ
ገዳጅ መመሪያዎችን አጠቃሎ ይዟል።በምን
ሠራዉ ሁሉ ሕግን ማክበር በጣም አስፈላጊ
ነዉ። በዚሕም ምክንያት የDW ሠራተኞች
በሙሉ የሚሠሩት ሕግን ጠብቀዉ ለመሆኑ፣
የንግድ (የሥራ) ምግባራችን ሁሉ ሥነ ምግብ
ራን የጠበቀ ለመሆኑ የሥነ ምግባር ደንቡ ማረ
ጋገጪያ ነዉ።

ሌሎች መሰረታዊ መመሪያዎች ደግሞ
በአሁኑ ጊዜ በድርጅቱ በአጠቃላይ እየተሰራበት
ያለው የDW አመራር እሴቶች ናቸው። የሥነምግ
ባር ደንብ እዚህ ጀርመን ውስጥና በዓለም ያተረፍ
ነዉን መልካም ስምና በጎ ዉጤት ጠብቀን ለማ
ቆየት ሲበዛ አስፈላጊ ነዉ። እነዚህ ደንቦች ምን
ያህል ወሳኝ እንደሆኑ፣ገቢር የሆኑ የውስጥ አሰ
ራሮች ምን እንደሚመስሉና እነዚህን አክብሮ መን
ቀሳቀስ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተልዕኮኣች
ንን ለማሳካት አብረውን ለሚሰሩ በሙሉ ለማሳ
ወቅ በማሰብ የተዘጋጀ ነው።

የሥነ-ምግባር ደንቡ በሁሉም ሠራተኞ
ችና ዶቼ ቬለ በስሩ በሚያስተዳድራቸዉ ልዩ ልዩ
ተቋማት ላይ በሙሉ ተፈፃሚ ነዉ። ደንቡን አክ
ብረን መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል። በተለይ ድር
ጅታዊ ባሕልና መርሁን በመቅረጽ ረገድ ከፍተኛ
ሚና የሚጫወቱት የድርጅቱ አመራርና አስፈጻሚ
አካላት ደንቡን ገቢር የማድረግ ልዩ ኃላፊነት አለ
ባቸዉ።

DW በመላዉ ዓለም የመናገር ነጻነትና
ሀሳብን በነፃነት የመግለጥ መብት እንዲከበር
የሚጥር መገናኛ ዘዴ እንደመሆኑ መጠን በራሱ
ዉስጥ የሚነሱ ፍትሐዊ ቅሬታና ተቃዉሞዎችን
የሚቀበልና የሚያስተናግድ አሰራርንም ፈጥረ
ናል። የሥነ ምግባር ደንቡን የሚጥሱ ማናቸዉ
ንም እርምጃዎች መርምረን አስፈላጊዉን እርምጃ
እንወስዳለን።

የናንተዉ
**ፔተር ሊምቡርግ**
ዋና ሥራ አስኪያጅ

# “የጋራ ራዕያችን እንጋራለን።

# የሥነ ምግባር ደንብ

የሥነ ምግባር ደንቡ ዶቼ ቬሌ ዉስጥ የሚሠራባቸዉን በጋራ ድርድር የተደረሰባቸዉን ስምምነቶች፣ የዶቸ ቬለን የዉስጥ መመሪያዎች እና ከሁሉም በላይ በዶቸ ቬለ የሥራ መመሪያ መፅሐፍ የተካተቱትን (መመሪያዎች)የያዘ ነዉ። እርግጥ ነዉ እነዚሕ ደንቦችና መመሪያዎች የሥ ነምግባር ደንቡ አካላት ሆነዉ ገቢራዊ መሆናቸዉ ይቀጥላል።

እንደ ሠራተኛ እራሳችንን ከነዚሕ ደንቦች ጋር የማስተዋወቅ ኃላፊነት ይጠበቅብናል። በየአንዳዱ ደንብ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች ካሉ ጥያቄዎቹን ለየሚመለከታቸዉ ሥራ አስኪ ያጆች፣የቅሬታ ሰሚ ኃላፊዎች እና ለየሚመለከ ታቸዉ ወገኖች ማቅረብ ይቻላል።

# የሚለየን
# ምድነው

### ስለራሳችን ያለን አመለካከት፣
### ያልወገነ መረጃ ለነፃ አዕምሮ

ተልዕኮአችን፣እንደገለልተኛ የጀርመን መገናኛ
ዘዴ ተቋም፣በመላዉ ዓለም ለሚገኙ ሰዎች ዜና
እና መረጃዎችን ማሰራጨት ነዉ፤ ሰዎቹ የየራሳ
ቸዉን አስተሳሰብ የመያዝ ነፃነታቸዉን እንዲጠ
ብቁ ማድረግ።
*Made for Minds.* (አዕምሮን አኅልባ ቾች)
ነን። ከተጠቃሚዎችና አጋሮቻችን ጋር በምናደር
ጋቸው ውይይቶች በዓለም ላሉ ጠያቂና አስተዋይ
አዕምሮዎች በአስተማማኝ መረጃ ላይ የተመሰ
ረቱ አዳዲስ አስተሳሰቦችን እናቀርባለን።
ከዚሕም ጋር ሰዎች የመማሪያ መሳሪያ ወይም
ሥልት እንዲኖራቸዉ ሁኔታዎችን በነፃ እናመቻቻ
ለን። የየራሳቸዉን አመለካከት በነፃነት እንዲያዳ
ብሩ ሐሳባቸዉን በነፃነት እንዲገልፁ በዉጤቱም
ግልፅ፣ ዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ በጋራ ለመፍ
ጠር እናግዝናለን።
እነዚህ በይፋ የሚታወቁ ግቦቻችን ናቸዉ። ግቦቻ
ችንን ገቢር የምናደርግባቸዉ ስልቶችም ከግቦቹ
እኩል ወሳኞች ናቸዉ።ከሌሎች ጋር የም ንጋ
ራቸዉ ግልፅ እሴቶች አሉን።ከራሳችን ስለሚ
ጠበቀዉም ሆነ እርስ በእርሳችን ስላለን መስተ
ጋብርም ጥርት ያለ ምስል አለን፡፡እነዚሕ በምር
ቶቻችንና በአገልግሎታችን ውስጥ (እንደ ድር)
ደርተዉ የዕለት- ከዕለት ዉሳኔዎቻችንና ባሕሪዎ
ቻችንን ይበይናሉ።

# “ሃሳቦችን በማካፈል ለጋራ ሰኬት እንጠቀምበታለን።

## ግልጽ ቁርጠኝነት ለነፃነት

ነጻነት፣ ዴሞክራሲ እና ሰብዓዊ መብቶች የጋዜጠኝነት ተግባራችን፣ የልማት መልዕክታችንና የማንነታችን ሥረ መሰረቶች ናቸው። የነጻነት እሴቶችን እናንፀባርቃለን።በየትኛዉም ሥፍራና ሁኔታ ገለልተኛና ግልፅ አቋም እንይዛለን፣ በተለይ ማንኛዉንም አይነት መገለልን፣ የፆታ አድልዎን፣ ዘረኝነትን ፀረ ሴማዊነትን እንቃወማለን።በጀርመን ታሪክ ምክንያት ለእስራኤል ልዩ ኃላፊነት አለብን።

## ግልጽ ውይይት፣አፅናፋዊ ትስስር

የጋዜጠኝነትም ሆነ የDW የማስተማር (DW Akademie) አገልግሎቶቻችን መሠረታዊ መርሆች የሰዎች ተጨባጭ ኑሮ፣ ሕይወትና ፍላጎታቸዉ ናቸዉ።ክፍት አስተሳሰባችንን፣ዓለም አቀፋዊና አሐጉራዊ ትስስሮቻችንን በመጠቀም በመላዉ ዓለም ከሚገኙ ሰዎች ጋር እንወያያለን። የተለያዩ ምርቶቻችንና አገልግሎቶቻችን በተፈለጉበት ጊዜና ቦታ ሁሉ አዳዲስ ግንዛቤዎችን ይፈጥራሉ። ገንቢ የሐሳብ ልዉዉጦችን እናበረታታለን፤ ሁሌምና የትም ሥፍራ፣ ሁሉንም ወገን በአክብሮት እናስተናግዳለን።

## በሳል ዕውቀት፣ ብዙሐዊ ምልክታዎች

ትልቁ ሐብታችን፤ብዝሐነታችንና የካበተ ልምዳችን ነዉ። ዓለምን በጥልቅ እናጤናለን፤ አበረታችና አዳዲስ መንገዶችን እንከተላለን፤ በሳል ጥያቄዎችን እንጠይቃለን እናም በመረጃ የተደገፉ፣ ከወገንተኝነት የፀዱ መልሶችን እንሰጣለን። የ160 ሐገራት ልሳነ-ብዙ ባልደረቦቻችን፣ ከተጠቃሚዎቻችንና ከአጋሮቻችን ጋር በመሆን ከፍተኛ ጥራት ያለው፤ ተገቢ፤ ወቅታዊና ሳቢ ይዘት ያላቸዉን ዝግጅቶችን ያቀርባሉ።

የነጻ መገናኛ ብዙኃን ሥርዓቶች እንዲጎለብቱ እናበረታታለን።መረጃን ለማድረስ፤ ለትምሕርትና ለነጻ ጋዜጠኝነት መመዘኛዎችን ወይም ደረጃዎችን እናወጣለን።ለጋራ ስኬቶቻችን የሚጠቅሙ ሐሳቦቻችንና ብዝሐነታችንን (ለሌሎች) አናጋራለን።

እነዚህ ዋና ዋና እሴቶች የሥነ-ምግባር ሕጎቻችን መሰረቶች ሲሆኑ ዉጤታማ ትብብርንና መከባበርን የሚያረጋግጡም ናቸዉ።

# ለሕግና ደንቦች ተገዢነታችን

የሥነ ምግባር መመሪያዉ ለሥራና አሰራር ባለዉ መመሪያ መሰረት በራሱ በDW ዉስጥ እና በቅርንጫፎቹ ያሉ የዕለት ከዕለት ግንኙነትና የጋዜጠኝነት ሥራዎች ይገዙበታል።ተዛማጅ ሕጎችና የኩ ባንያዉ ልዩ ደንቦች በሥነ ምግባሩ አካል ሆነዉ ገቢር መሆናቸዉ ይቀጥላል።

አስተዳዳሪዎችና ሥራ አስፈፃሚዎች ምሳሌ በመሆናቸዉ ለሥነ ምግባር ደንቡ ተገዢ መሆናቸዉን በገቢር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

DW፣ ሠራተኞቹ ለሚከተሉት ነጥቦች ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ይጠብቃል።ደንቦቹን መጣስ በሥራ-አሰሪ ደንብ መሰረት ያስቀጣል።

## በአጠቃላይ የእኩልነት ደንብ (Allgemeines Gleichbehandlungsgesetz (AGG)) መሠረት በአድሎ ላይ የተጣለ ገደብ

በAGG መሰረት የፆታ አድልዎ (ጫና)፣ ዘረኝነት እና ፀረ ሴማዊነትን ጨምሮ ማንኛዉም ዓይነት አድልዎ በእርስ በርስ ግንኙነታችንም ሆነ በአገልግሎታችን ዉስጥ ማንፀባረቅ ምሕረት የለዉም።በሥራችን ምክንያት የምንገናኘዉን ማንኛዉንም ሠራተኛ፣ ደንበኛ ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገንን በፀ ረሴማዊነት፣ በዘረኝነት መንፈስ ወይም በጎሳ፣ በፆታ፣ በሃይማኖት ወይም በርዕዮተ ዓለሙ (አመ ለካከቱ)፣ በአካል ጉዳተኝነቱ ወይም በዕድሜና በፆታዉ ምክንያት ጨርሶ ልናገልለዉ አይገባም። በደቦም ሆነ በተናጥል ማስፈራራትንና ወሲባዊ ጥቃትን አጥብቀን እንቃወማለን።በተወሰኑ ሰዎች ወይም በግለሰብ ላይ ስድቦችንና አሉባል ታዎችን ማሰራጨትም ክልል ነዉ።

በጎሳና በዘር ላይ የሚሰነዘሩ ጥላቻዎችን፣ ሆሎካዉስትን መካድ ወይም ማነፃፀርን የመሳሰሉ ሕገ ወጥ ባሕሪዎችን ጨርሶ አንታገስም።

## ሐሳብን በነፃነት የመግለፅ ገደቦች

የደቦ ማስፈራራት፣ የፆታ ጥቃት፣ በሐሰትና ባሉባልታ የሰዎች ስም ማጥፋት ሲከተል ሐሳብን በነፃነት የመግለፅ መብታችን መስመር ማለፉን እናዉቃለን።ሐሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ሆሎኮዉስትን መካድንና ማነፃፀርን እንደማይጨመርም እናዉቃለን።

የDW ተቀጣሪ እንደመሆናችን መጠን በማኅበራዊ መገናኛ ዘዴዎችና በሌሎች ሕትመ ቶችና (ፕሮግራሞች) ይዘት ላይ ጥንቃቄ የማድረግ ግላዊም ሙያዊም ሐላፊነት አለብን።ይሕ ጥንቃቄ ለDW እና ለሥራችን እሴቶች ካለብን ኃላፊነት፣ እንደቀጣሪ ለDW እና በቅጥር ስም ምነታችን ላይ በተጠቀሰዉ መሰረት ለሌሎች ተቀጣሪዎች (ባልደረቦቻችን) ካለን ታማኝነት የሚነጭ ነዉ።

ከሥራ ዉጪ በሚኖረን ግንኙነት በግልፅ የምናደርገዉ እንቅስቃሴ ያለብን ኃላፊነት፣ ሙያዊ እንቅስቃሴን የማይዘነጋ፣ የDWን አቋምና ፍትሐዊ ጥቅሙን የማይቃረን መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለብን።ምን ጊዜም እና በየ ትኛዉም አጋጣሚ ቢሆን አድሏዊ፣ ፆታዊ ጫናን አመልካች፣ዘረኛና ፀረሴማዊ አስተያየቶችን ከመ ስጠት መታቀብ አለብን።እንዲሕ ዓይነት አስተያየ ቶች በአሰሪና ሠራተኛ ደንብ መሰረት ከሥራ እስከ መባረር የሚደርስ ቅጣት ሊያስከትል ይችላል።

እንደ ሠራተኛ እኛን የሚመለከቱ መሠረታዊ ሕጎችን፣ የጋራ ስምምነቶችን፣የDW የዉስጥ መመሪያዎች በተለይም በDW የሥራ መመሪያ መፅሐፍ የተጠቀሱትን ደንቦችን እናዉቃለን።እናከብራልነም።እነዚሕ ደንቦችና መመሪያዎች ገቢራዊ መሆናቸዉን ይቀጥላሉ።በየትኛዉም ሁኔታ በሥነ ምግባር ደንቡ አይሻሩም።

“ በእርስበርስ ግንኙነትም ሆነ በምናቀርባቸው ሥራዎች ማግለልን አንታገሰም።

# የርስበርስ ግንኙነታችን መሰረቶች

### መከባበር

በሐቀኝነትና በመከባበር መንፈስ አብረን እንሠራለን።
እያንዳንዱን ሰው፤ ብሔር ፣ሃይማኖት፣ የአካል ጉዳት፣ዕድሜ ወይም ጾታዉ ሳይገድበን እናከብራለን።
ለሐሳብ ልዩነት ዋጋ እንሰጣለን።
በሥራ ቦታ የሚፈጸም ጾታዊ ትንኮሳን በፍጹም የማይታገስ መርሕ እንከተላለን።
በየትኛዉም መንገድ የሚፈፀም ሥልጣንን አላግባብ መጠቀምን ጨርሶ አንታገስም።

**“ ግልፅ እና የምንለውን ነው።**

### ግልጽነትና ትብብር

መረጃን በግልጽና በፍጥነት እናጋራለን።
የቦታ እና የሥራ ክፍሎች ልዩነት ሳይገድቡን በጋራ እንሰራለን።
አዳዲስ ሀሳቦችና ፈጠራዎችን ለመቀበል ዝግጁ ነን። ከተስማማንባቸዉ ግቦች ጋር የሚጣጣም መከባበር፣ ግልጽነት እና ትብብር፣ መተማመን፣ታማኝነት፣ ገንቢ ግብረ መልሶች እንዲሁም የአመራር እና የሥራ ባሕል፤ የሥራችን የማዕዘን ድንጋዮች ናቸው።

### ዕምነት

ግልጽና ዕውነተኞች ነን።
ለተቀበልናቸዉ ኃላፊነቶች ቅንና ታማኞች ነን።
ለግልጽ የሐሳብ ልዉዉጥና ለሒሳዊ ግብረ መልሶች የሚመች የስራ ድባብ እንፈጥራለን።

## የገንቢ ግብረመልስ ባህል

እየተሰራባቸው ያሉ ልምዶችን በማሻሻል፣ አዳዲስ አቀራረቦችን በመፍጠር በራሳችን ምግባራት ወይም ባሕሪዎችን በመገምገም የገንቢ ግብረ መልስ ባሕልን እንመሰርታለን (እንፈጥራለን)፡፡

ስህተቶችን እንደ መሻሻያ አጋጣሚዎች እንጠቀምባቸዋለን፡፡

ሰዎች በሂደት ለውጥ ለማምጣት እንደሚችሉ እና ሃሳባቸውን እንደሚቀይሩ እርግጠኞች ነን፡፡

ቅራኔዎችን እናስተናግዳለን፤ እንፈታለንም፡፡

ስለ DW ተወካዮች፣ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሐሰት ወሬዎችን እንነዛም፡፡

## ታማኝነት

የ DW ን እሴቶችና የአሰራር ስልቶችን እናከብራለን፡፡

ለዉጦችን ገቢር በማድረጉ (በመቅረፁ) ሂደት በንቃት እንሳተፋለን፡፡

በታማኝነትና በፅናት ለማገልገል ቁርጠኞች ነን፡፡

## ግብ-ተኮር ምግባር

የ DW ግቦችን ለማሳካት በገለልተኝነት እንሠራለን፡፡

ተነሳሽነትንና ፈጠራን ለማበረታታት አዳዲስ ሐሳቦችን እንጠቀማለን፡፡

ዉጤት ተኮር ነን፡፡



# ከአጋሮችና ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ያለን ግንኙነት

## የአዕምሮ ውጤቶች ባለቤትነት

ስለ አዕምሮ ውጤት ባለቤትነት በሚደነግግዉ ደንብ መሠረት፣ የሦስተኛ ወገኖችን የአዕምሮ ሐብት እናከብራለን፤ እንጠብቃለንም።

## የጥቅም ግጭቶች

የሥራና የንግድ ጉዳዮችን የምንወስነዉ የDWን ጥቅም በሚያስከብር መልኩ ነዉ። የግል ጥቅምና ግንኙነት የሚያሳድርብን ተፅዕኖ የለም።

የጥቅም ግጭቶች ሊኖሩ በሚችሉበት ወቅት ጉዳዩን በንቃት እናሳዉቃለን።

የንግድም ሆነ የፕሮጀክት አጋሮቻችን ምንም ዓይነት የጥቅም ግጭት እንደሌለባቸው እናረጋግጣለን።

## ሙስናና (ኃላፊነትን) አለአግባብ መጠቀም

በየትኛዉም መንገድ የሚገለጥ ሙስናን እንቃወማለን፣ በየትኛዉም መንገድ የሚታዩ የሙስና ፍንጮችን እናስወግዳለን።

ማንኛውንም ዓይነት ውለታ፣ጉቦ ወይም የግል ፍላጎትን ለማርካት የሚደረጉ ማናቸዉም ዓይነት ጥቅማጥቅሞችን እንቃወማለን።

## የሥራ አጋሮች

የሥራ አጋሮቻችንን ስንመርጥ የDWን እሴቶች መግለጫ እንጠቀማለን።

“ የንግድ ውሳኔዎችን የምናደርገው በDW ጥቅሞች መሠረት ነው።

### ስጦታዎችና ጉርሻዎች

ገለልተኝነታችንን የሚያጠራጥሩ፤ በተጨባጭ እዉነታዎች ላይ ያልተመሰረቱ ንግድ-ነክ ዉሳኔዎችን እንድንሰጥ የሚያደርጉ ስጦታዎችን፤ግብዣዎችን እና ለጋዜጠኞች የሚሰጡ አበሎችን አንቀበልም።

ሌሎች ስጦታዎችን፣ ግብዣዎችንና ጥቅማጥቅሞችን የምንቀበለው፣በፍፅም ግልፅነትና አግባብ ካላቸዉ ሕግጋትና ዉስጠ-ደንቦች ጋር የማይቃረኑ እስከሆኑ ድረስ ብቻ ነዉ።

ግብዣዎችንና ስጦታዎችን የምናቀርበው በጣም በተወሰኑ ተገቢ ምክንያቶች ብቻ ነዉ። የተገቢትነቱ ጥያቄ የሚበየነዉ፤ ምንም እንኳን ጉዳዩ የሚከናወንበት ሐገር አስተሳሰብ ከግምት ዉስጥ ቢገባም፤ በጀርመን አስተ ሳሰብና ግንዛቤ ነዉ።

### የዕቃ ግዢ እና ጨረታ

ምርቶችን፣አገልግሎቶችን እና ሸቀጦችን (ዕቃዎ ችን) የምገዛዉ አግባብ ባለዉ ሕግና በመስሪያ ቤቱ ደንብ መሰረት፣ ጥራትን፣ ዋጋን የገበያ ዉድድርን ጠብቀን ነዉ። የግዢ ዉሳ ኔዎች የሚደረጉት አቅራቢዎች ያመጧቸውን ምርቶች እና አገልግሎቶች ጥራትን በተጨ ባጭ ካረጋገጥንና ካወዳደርን በኋላ ነዉ። ተመናቸዉ በገበያ አቅርቦትና ተጠቃሚነት ላይ ተመስርቶ የሚለዋጥ የግዢ ዉል እን ፈፅምም።

# የመረጃ አያያዛችን

## ምስጢራዊነት

የንግድ ምሥጢሮችንና ምሥጢራዊ መረጃዎ ችን በከፍተኛ ጥንቃቄ እንይዛለን። ይህም በዝግጅቶቻችን (ርዕሰ-አንቀፅ) ይዘትና ይፋ ሊደረጉ በማይገቡ ሌሎች መረጃዎች ላይም ገቢራዊ ይሆናል (ይፀናል)።

ምሥጢራዊ መረጃዎች፣ ምንም እንኳን በዲጂታል ቅርፃቸዉ ቢታዩና፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ ባልደረቦቻችን የሚያዉቋቸዉ ቢሆኑም ምሥጢራዊነታቸዉ እንደተጠ በቀ ነዉ።



## የመረጃ ጥበቃ

የምንሰበስበው አስፈላጊ የሆነ መረጃን ብቻ ነው (የመረጃ ምጣኔ)።

በሕግ በተፈቀደው የመረጃ አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና የግል መረጃ አተናተን መሰረት ምሥጢራዊነትን በመጠበቅ መረጃው አግባብ ባልሆነ መንገድ እንዳይወጣ ብርቱ ቁጥጥር እናደርጋለን።

መረጃውን የምናስቀምጥበትና በተለየ ኮድ ለመሰደር (ለመመስጠር) ስንወስን ምሥጢራዊነቱን እናከብራለን።

## ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT)ና የመረጃ ደኅንነት

በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT) ሥርዓት ስንሰራ፤ ሥርዓቶቹን አላግባብ ከመጠቀም ለመከ ላከል፣ የIT መመሪያዎችን በማክበር የIT እና የመረጃ ደሕንነትን በዉስጥም ሆነ በዉጪ ሥራችን ገቢራዊ እናደርጋለን።

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በንዝህላልነት መጠቀም በ DW የመረጃ ደኅንነት ላይ ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ስለምንገነዘብ ተገቢውን እርምጃ እንወስዳለን።



**“ መረጃን በጥንቃቄ እንይዛለን።**

# ከሕዝብ ጋር
# ያለን ተግባቦት





## “ እንደ ግለሰብ ወይም እንደ DW ተቀጣሪ እየተንቀሳቀሰን ወይም እየሠራን እንደሆነ ግልጽ እናደርጋለን፡፡


ስለ DW አጠቃላይ አሰራር ከጋዜጠኞችና (ከሌሎች)መገናኛ ብዙኃን ድርጅቶች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የተናጠል መልስ አንስጥም። ጠያቂዎችን የመረጃ ፍሰትን ለሚያቀናብረዉና ለሚያስተዳድረው ከድርጅቱ የደንበኞች (የህዝብ) ግንኙነት ክፍል ጋር እናገናኛቸዋለን፡፡በሚኖሩን ግንኙነቶች ሁሉ የምናደ ርገዉ እንቅስቃሴ በግል ወይም እንደ DW ሠራተኛ መሆን-አለመሆኑን ግልፅ ማድረግ አለብን።

በሁሉም ግንኙቶች እንደ ግለሰብ ወይም DW ተቀጣሪ እየተንቀሳቀስን ወይም እየሠራን እንደሆነ ግልጽ እናደርጋለን።

ሊከሰቱ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶችን ለማስወገድ፣ ከሥራ ውጭ በምናደርጋቸውና በሕዝብ ላይ ተጽእኖ ሊኖራቸው በሚችሉ ጉዳዮች ላይ የውስጥ አሰራራችን በሚፈቅደው የአሰራር ደንብ መሰረት ብቻ እንንቀሳቀሳለን።

# የደኅንነትና ዘላቂነት መስፈርታችን

“ ዘላቂነት ባለው መልኩ እንሠራለን።




የሥራ ቦታ የጤናና የደሕንነት መመሪያዎችን
እናከብራለን።

ቀዉስ ባለባቸው ቦታዎች ስምሪት ሲደረግ
ደንባችንን እንከተላለን።


ቁሳቁሶችን ዘላቂ በሆነ መንገድ እንጠቀማለን፣
በተለይም ያሉንን ሀብቶች ለአካባቢ
ጥበቃ ተስማሚ፣ ቆጣቢ በሆነና ዳግም
በጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስችል መልክ
መጠቀማችንን እናረጋግጣለን።

ሥራችን ወይም ርምጃችን በአጋሮቻችን ላይ
ያልታሰበ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን
እናረጋግጣለን።



# የድርጅቱን ንብረት የምንይዝበት መንገድ

የመሥሪያ ቁሳቁሶችንና ሌሎች የDW ንብረቶችን
በጥንቃቄ እንይዛለን።
የሥራችንን ውጤት ለDW እናደርሳለን።
የመስሪያ ቁሳቁሶችን ስንገለገል የቁጠባንና
በአግባብ የመስራት መርሆዎችን እንከተላለን።



**“ ቅልጥፍና እና ቁጠባን እናሰተውላለን።**


Made for minds.

# የጋዜጠኝነት (editorial) መርሆችና መሰፈርታችን

- በሕዝብ አስተሳሰብ ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር ረገድ ያለብንን ኃላፊነት ስለምናውቅ ፤ ጠንቃቆች ነን።
- ሥራችንን የምናከናዉነዉ የ DW ን ሕግ በመከተል ነው።
- እንደ ጋዜጠኛ በገለልተኝነት መንፈስ እንሰራለን፤ በሦስተኛ ወገን ፍላጎት ተፅኖ ስር አንወድቅም።
- ከብዝሐነትና ከስብጥር አመለካከቶች የሚመ ነጩ የሐሳብ ልዩነቶችን እናከብራለን።
- መረጃዎችን በምናጠናቅርበት ወቅትም ሆነ ስንዘገብ፣ የጋዜጠኝነት መርሕን፣ ሥነምግባር ንና ኃላፊነት እናከብራለን፣ በበሰለና ሚዛና ዊነቱን በጠበቀ መንገድ እንዘግባለንም።
- የማስታወቂያንና የፕሮግራሞችን ይዘት የሚለየዉን ገዢ ሕግ እናከብራለን።
- የሰዎችን ግላዊ ምሥጢር የማብከርና መረጃን፣ አስተያየቶችንና ምስሎችን (ፎቶዎችን) በትክክለኛው መንገድ የመያዝ ደንቦችን በጥብቅ እናከብራለን።
- DWን የማኅበራዊ መገናኛ ዘዴዎችና የዋና አርታኢውን የጋዜጠኝነት መመሪያዎች እናከብራለን።



“ የጋዜጠኝነት
መርሆዎችን በንቃት
እናከብራለን።

# የምን-ምግባር ደንቡን

# የመተግበር መመሪያዎች

## የDWን ደንብ መጣስ የሚያስከትላቸው

የሥነ ምግባር ደንቡ ተጥሶ ሲገኝ፣ ለወደፊቱ ሌላ ደንቡ እንዳይጣስ ለመከላከ ልና ግልፅ ለማድረግ የሚረዱ አስፈላጊ ርምጃዎችን DW ይወስዳል። ከነዚሕ እርምጃዎች የመጀመሪያዉ የሚመለከተዉ (ደንቡን የጣሰዉ) ሠራተኛ ሥለጣሰዉ ደንብ ምንነት እንዲያዉቅና የባሕሪ ለዉጥ እንዲያደርግ ከሠራተኛዉ ጋር ዉይይት ማድረግ ነዉ። ደቡን በጣሰዉ ሠራተኛ ላይ በሠራተኛ ሕግ መሰረት የሚወሰድበት እርምጃ የሚወሰነዉ በጣሰዉ ደንብ ደረጃ ወይም መጠን ነዉ።ይሕ ቅጥርን ወይም የአገልግሎት ግንኙነትን እስከማቋረጥ ሊደርስ ይችላል።

## የሚከተሉት ጥያቄዎች የሥነ-ምግባር ደንቡን ለማክበር ሊረዳዎት ይችላሉ

ተገቢዉን ሕግና የድርጅታዊ መመሪያዎችን እያከበርኩ ነው?
ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ወገኖች ጋር አስቀድሜና በተገቢዉ ሰዓት የሚደረጉ ዉሳኔዎችን አቀናጅቻለሁ?
የማሳልፋቸው ውሳኔዎች የDWን ጥቅም ብቻ የሚያስከብሩና ከግል ጥቅሜ የፀዱ ናቸዉ?
ውሳኔዬ ሊኖረው የሚችለው ውጫዊ ተጽዕኖ ምንድ ነው? ዉሳኔዬ የሦስተኛ ወገን ግምገማን ያልፋል? የDW ን መልካም ስምስ ያስጠብቃል?
ውሳኔዬን ከራሴ ሕሊና ጋር ማስታረቅ እችላለሁ?

ለሁሉንም ጥያቄዎች ያለምንም ማወላወል ‹‹አዎ›› ብለው መመለስ ከቻሉ ፣ ውሳኔዎ ከሥነ-ምግባር ደንቡ መርሆዎች ጋር የሚጣጣም ነዉ። እርግጠኛ ካልሆኑ ግን ከዚሕ በታች የተዘረዘሩት ሰዎች ሊረዱዎት ይችላሉ።

# ማንኛውም ጥያቄ ካለዎ

# ሊያገኟቸው የሚችሉ ሰዎች



**የሥነምግባር ደንቡን በመከተል ረገድ እርግጠኛ ያልሆኑበት ነገር ካለ ወይም ማንኛዉም ጥያቄ ካለዎት እባክዎ፣ የቅርብ ኃላፊዎን ወይም የሥነምግባር ተጠሪዉን (ኦፊሰሩን) ያናግሩ።**



## የደንብ መተላለፍ ሲያጋጥም የሚያማክሯቸዉ ሰዎች

የሥነ ምግባር ደንቡ በሁሉም የDW ሠራተኞች ላይ ተግባራዊ ይሆናል።
በድርጅታችን ውስጥ ደንቡ ሲጣስ ካስተዋሉ፣ መጀመሪያ ትክክለኛ ባሕሪ አላሳየም (ደንቡን ጥሷል) ብለዉ የጠረጠሩትን ሰዉ በቀጥታ ማናጋገር አስፈላጊ ነው።የሥነ ምግባር ደንቡን እርስዎ ራስዎ ከጣሱ እኛን ያግኙን (ለኛ ያሳዉቁ) እንደ ጥፋቱ ዓይነት ጉዳዩን ለቅርብ ኃላፊዎ ወይም ለሥነምግባር ጉዳይ ተጠሪ፣ ለAnnelie Gröniger:
compliance@dw.com ወይም በ+49.228.429-2105 ሊያሳውቁ ይችላሉ።

ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው በተለይም የሠራተኞች ተወካዮች ወይም አስፈላጊ ከሆነ የዉጪ የጸረ-ሙስና መስሪያ ቤት ኃላፊ ወይም ከጾታዊ ጥቃት ለመከላከል የሚሰሩ ተቋማትና ተጠሪዎችን ማናገር ይቻላል።

ለየትኛዉም ወገን ቢያመለክቱ፣ ማመልከቻዎ ወይም ጥቆማዎ በከፍተኛ ምሥጢር እንደሚጠበቅ እርግጠኛ መሆን ይችላሉ።

## ደንቡ ሲጣስ DW የሚወሰዳቸዉ እርምጃዎች

ደንቡ ሲጣስ፣ DW አስፈለጊዉን እርምጃዎች ይወስዳል። መጀመሪያ፦-ጉዳዩ የሚመለከተዉ (ደንቡን የጣሰዉ) ሠራተኛ ያስተሳሰብ ለዉጥ እንዲያመጣ ፤አግባብ ባለዉ በዚሕ ደንብ መሠረት የሥነ-ምግባር ደንቡን እንዲገነዘብ ገለፃና ማብራ ሪያ ይደረግለታል። ደንቡን የጣሰ ሠራተኛ፣ አግባብ ባለዉ መመሪያና በአሰሪና-ሠራተኛ ሕግ መሰረት የቅጥር ደረጃዉ ሊለወጥ ይችላል።

ከኅዳር 2022 ጀምሮ | © DW